የፌደራል መንግስት

# የሴት ልጅ ግርዛት

## ጥበቃ ደብዳቤ

ከሀገር ውጪ በሚጓዙበት ጊዜ ይህን የጥበቃ ደብዳቤ ይዘው መጓዝ አለብዎት። ጀርመን ውስጥ የሴት ልጅ ግርዛት የብዙ አመት የእስር ቤት ቅጣት የሚያስከትል ወንጀል መሆኑን ለቤተሰብዎ በግልጽ እንዲያሳዩ ያስችልዎታል።

የጀርመን ፌደራላዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግስት

**የሴት ልጅ ግርዛት ወንጀል ነው** እንዲሁም ለተጎዱ ሴት ልጆች እና አዋቂዎች የእድሜ ልክ፣ ከባድ አካላዊ እና አእምሯዊ ውጤት ያለው አሰቃቂ የሰብአዊ መብት ጥሰት ነው። የሴት ልጅ ግርዛት ተግባር ከፍተኛ የደም መፍሰስ እና ከባድ ማመርቀዝ ስለሚያመጣ በቀጥታ ሞት ሊያስከትል ይችላል።

**ጀርመን ውስጥ፣ የሴት ልጅ ግርዛትን ማካሄድ በህግ የሚያስቀጣ ጥቃት ሲሆን እስከ 15 አመት በሚደርስ እስራት ያስቀጣል።**

የሴት ልጅ ግርዛት ማለት ውጫዊውን የሴት ብልት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ነው፤ በጣም ከባዱ አይነት ደግሞ፣ የሴት ልጅ ብልት ክፍተቱን ሙሉ ለሙሉ በሚባል ሁኔታ ተሰፍቶ ይዘጋል።

## በዚህ ደብዳቤ ምን አደርጋለው?

ይህን የጥበቃ ደብዳቤ ከእርስዎ ጋር መውሰድ ይችላሉ እናም በሀገር ቤትዎ ለቤተሰብዎ ያሳዩ። ደብዳቤው ጀርመን ውስጥ የሴት ልጅ ግርዛት ማካሄድ **በህግ የሚያስቀጣ ጥቃት** መሆኑን ይገልጻል– ከሀገር ውጪ የሚደረግ ቢሆንም። እርስዎ ራስዎ የሴት ልጅዎ ላይ ግርዛት ከፈጸሙ ወይም የሴት ልጅ ግርዛቱን ሌላ ሰው ካደረገው እና ይህ እንዳይፈጠር ካልተከላከሉ ወይም በሂደቱ እገዛ ካደረጉ እስከ **15 አመት እስር** ይጠብቅዎታል። ወደ ጀርመን እንዳይገቡ ሊከለከሉ ወይም የመኖሪያ ፍቃድዎን ሊያጡ ይችላሉ።

# በህግ የሚያስቀጣ ወንጀል (የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 226a)

በጀርመን ህግ መሰረት፣ የሴት ልጅ ግርዛትን ማከናወን በህግ የሚያስቀጣ ወንጀል ነው (የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 226a)። የሴት ልጅ ግርዛትን የሚያከናውን ማንኛውም ሰው በህግ የሚያስቀጣ ወንጀል እየፈጸመ ነው እናም እስከ 15 አመት የእስር ቅጣት ይጠብቀዋል።

የሴት ልጅ ግርዛት **ከሀገር ውጪ** የሚደረግ ከሆነ ወይም የሚያከናውነው ሰው ጀርመናዊ ከሆነ፣ ወይም የሴት ልጅ ግርዛት የተፈጸመባት ሴት ልጅ ወይም አዋቂ ሴት ጀርመናዊ ከሆነች ወይም ጀርመን ውስጥ ዋና የመኖሪያ ቦታ ካላት በህግ ያስቀጣል።

የሴት ልጅ ግርዛት ሲካሄድ ጀርመን ውስጥ ወይም ከሀገር ውጪ ሆኖ የሚረዳ ማንኛውም ሰው በወንጀል የሚያስቀጣ ጥቃትን እየፈጸመ ነው።

ሌሎች የሴት ልጅ ግርዛትን እንዲያከናውኑ የሚያሳምን ማንኛውም ሰው በወንጀል የሚያስቀጣ ጥቃትን እየፈጸመ ነው።

ይህ ጀርመን ውስጥ ወይም ከሀገር ውጪ ሴት ልጆቻቸው የሴት ልጅ ግርዛትን እንዳያደርጉ የማይጠብቁ ወላጆችን ያካትታል።

የሴት ልጅ ግርዛት የተፈጸመባት ሴት ልጅ ወይም አዋቂ ሴት ተጠያቂ አትሆንም እንዲሁም አትቀጣም።

የሴት ልጅ ግርዛትን የሚያካሂዱ፣ ሌሎች እንዲረዷቸው የሚያሳ ምኑ ወይም ሴት ልጆቻቸውን መጠበቅ የተሳናቸው ሰዎች በተጨ ማሪም የመኖሪያ ፈቃድ መብታቸውን ሊያጡ እና ወደ ጀርመን እንዳይገቡ ሊከለከሉ ይችላሉ።

## የሴት ልጅ ግርዛት ምንድን ነው?

የሴት ልጅ ግርዛት አሰቃቂ የሰብአዊ መብት ጥሰት ሲሆን ውጫዊው እና/ወይም ውስጣዊው ከንፈር እና ክሊቶሪስ የተወሰነው ወይም ሁሉም ሲወገድ እንዲሁም (በጣም አስከፊው አይነት) የሴት ብልት ሲሰፋ ነው፤ በተወሰኑ ሁኔታዎች የስፒል ጫፍ የሚያክል ቀዳዳ ብቻ ይተዋሉ። ሴቶቹ በሂደቱ ጊዜ ብዙ ደም ይፈሳቸዋል ወይም ቁስሉ ሊያመርቅዝ ይችላል፤ ይህም ከባድ የጤና ቀውሶች እንዲሁም ሞት ሊያስከትል ይችላል።

- የእድሜ ልክ ህመም፣ የአእምሮ ቀውስ
- የወሊድ ችግሮች፣ ስር የሰደዱ ማመርቀዞች
- የስሜት ህመሞች እና በወሲባዊ ግንኙነት ጊዜ ህመም

የሴት ልጅ ግርዛት የተፈጸመባቸው ሴቶች የሚሰቃዩት ከእድሜ ልክ ህመም፣ የአእምሮ ቀውስ እና ከወሊድ ችግሮች ብቻ አይደለም። ስር በሰደዱ የኩላሊት ማመርቀዞች ወይም የሽንት ከረጢት ማመርቀዞች ሊታመሙ ይችላሉ እናም ህመም በበዛበት የወር አበባ ጊዜ ይሰቃያሉ።

አካላዊ እና አእምሯዊ ጉዳቶች የአዋቂ ሴቶች እና የሴት ልጆችን ወሲባዊ ሁኔታዎች ላይ በራስ የመወሰን መብትን በአሰቃቂ ሁኔታ ይጥሳሉ። ወሲባዊ ግንኙነት በጣም ከፍተኛ ህመም ያለው ነው፤ ወሲባዊ ስሜቶች በነርቭ መጥፋት ምክንያት በጣም ይቀንሳሉ ወይም ይጠፋሉ።

አንዴ ከተፈጸመ፣ የሴት ልጅ ግርዛትን ብዙ ጊዜ መመለስ አይቻልም።

# እርዳታ የት አገኛለው?
# FGM ይካሄዳል ብዬ ከጠረጠርኩ ምን አደርጋለው?

እርስዎ ወይም እርስዎ የሚያውቁት ሰው ለ FGM ወደ ሌላ አገር የመወሰድ አደጋ ውስጥ ነው ወይም ጀርመን ውስጥ እንደዚህ አይነት አደጋ አለ ብለው ከሰጉ፣ የሚከተሉትን ማነጋገር ይችላሉ

- **ፖሊስ (ስልክ ቁጥር፡- 110) ወይም**
- **የአካባቢዎ የወጣቶች ደህንነት ቢሮ።**

**ብሄራዊ የሴቶች ጥቃት የእርዳታ መስመር በስልክ ወይም በኦንላይን ድጋፍ ይሰጣል።**

HILFE TELEFON
GEWALT GEGEN FRAUEN
08000 116 016

- **ስልክ ቁጥር፡-** 08000 116 016
- www.hilfetelefon.de

**የእርዳታ መስመሩ በ 18 ቋንቋዎች – 24/7፣ በነጻ እና በሚስጢር ምክር ይሰጣል።**

**ከሀገር ውጪ ከሆኑ እና እርዳታ ከፈለጉ አቅራቢያዎ ያለ የጀርመን ዲፕሎማቲክ ልኡክን ማነጋገር ይችላሉ።**

**ጀርመንኛ፡-**
www.auswaertiges-amt.de/de/ReiseUndSicherheit/deutsche-auslandsvertretungen

**እንግሊዘኛ፡-**
www.auswaertiges-amt.de/en/aussenpolitik/laenderinformationen

የሴት ልጅ ግርዛት ጥበቃ ደብዳቤ የጀርመን ፌደራላዊ ሪፐብሊክ 2023

Federal Ministry for Family Affairs, Senior Citizens, Women and Youth

Lisa Paus
Federal Minister for Family Affairs, Senior Citizens, Women and Youth

Federal Ministry of the Interior and Community

Nancy Faeser
Federal Minister of the Interior and Community

Federal Foreign Office

Annalena Baerbock
Federal Minister for Foreign Affairs

Federal Ministry of Justice

Marco Buschmann
Federal Minister of Justice

Federal Ministry of Health

Karl Lauterbach
Federal Minister of Health

**ምልክት**

**ይህ የጥበቃ ደብዳቤ የፌደራል መንግስት የህዝብ ግንኙነቶች ስራ ክፍል ነው፤ ከክፍያ ነጻ እንዲሆን ያደርጋል እና የሚሸጥ አይደለም።**

**በፌደራል መንግስቱ ምትክ የታተመው በ፡-**
Bundesministerium
für Familie, Senioren, Frauen und Jugend
Referat Öffentlichkeitsarbeit
11018 Berlin
www.bmfsfj.de

**ማንኛውም ጥያቄዎች ካልዎት፣ በሚከተለው**
**የአገልግሎት ስልክ ይደውሉልን፡-** +49 30 20 179 130
**ከሰኞ እስከሐሙስ፡-** 9 am – 6 pm
**ፋክስ፡-** +49 30 18 555-4400
**ኢሜይል፡-** info@bmfsfjservice.bund.de

**ለሁሉም ኤጀንሲዎች እና መስሪያ ቤቶች የሚሆን የህዝብ አገልግሎቶች ስልክ ቁጥር፡-** 115*

**ከ፡- ጥር** 2023 **ጀምሮ፣ 4ኛ እትም** (amharisch)
**ዲዛይን፡-** www.zweiband.de
**አታሚ፡-** MKL Druck GmbH & Co. KG

* ለሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች እና ኤጀንሲዎች ላልዎት ጠቅላላ ጥያቄዎች፣ በህዝብ አገልግሎት መስጫ ቁጥር 115 ይደውሉ። በሚሳተፉ ክልሎች ውስጥ፣ 115 ከሰኞ እስከ አርብ ከ 8 am እስከ 6 pm ክፍት ነው። ከጀርመን መስመር ወደ 115 የሚደረጉ ጥሪዎች እና ብዙ ተንቀሳቃሽ አውታረ መረቦች በአካባቢው ተመን ይከፍላሉ እንዲሁም ለወጥ ተመን ተጠቃሚዎች ከክፍያ ነጻ ናቸው። መስማት የተሳናቸው ሰዎች የ SIP አድራሻው 115@gebaerdentelefon.d115.de። ላይ በመደወል መረጃ ማግኘት ይችላሉ። በክልልዎ 115 እንዳለ ለማወቅ እና ስለ ጠቅላላ የህዝብ አገልግሎት ቁጥር የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ http://www.d115.de ድህረ ገጽን ይጎብኙ።